# ክፍለ ትምህርት አንድ

## መሪዎችና ተከታዮች

በዚህ ክፍለ ትምህርት በእግዚአብሔር የተመረጡ መሪዎችን ምሳሌነት በመመልከት መንፈሳዊ መሪዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑና የእግዚአብሔርንም ዓላማ ከግቡ ለማድረስ እንዴት ከሌሎች ጋር ተስማምተው መሥራት እንደሚገባቸው እንመለከታለን፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ
- የዮሴፍ ምሳሌት
- የመሪነት ባሕሪያት

---

### የክፍለ ትምህርቱ አላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፡፡

- መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ስላላቸው ሥፍራ መግለጽ
- በመሪነት አገልግሎታቸው የተሳካላቸውን ሰዎች ባሕርይ መዘርዘር
- ከመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎችም የሕይወት ገጽታዎች የመሪነት ባሕርያት ምሳሌ መሆን የሚችሉትን ለይቶ ማወቅና መግለጽ

---

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1/ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የተጻፈውን በጥንቃቄ አንብብ። ተከታታይ ትምህርቶቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ መከታተል እንድትችል ይረዳሀል።

2/ ትምህርቱን በማንበብ ለጥናት ማጠናከሪያ የተሰጡትን ጥያቄዎች እንድትመልስ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄና በማስተዋል ማንበብህን አረጋግጥ፣ ይህም ትምህርቱን እንደሚገባ ለመረዳት እንድትችል ይረዳሀል።

3/ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የቀረበውን የሙከራ ፈተና ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

## የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ

## መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ

*የመንፈሳዊ መሪዎች መኖር ለምን እንዳስፈለገ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ረጋ ብለን በመጠየቅ ብንጀምር፣ ሁለት ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሰዎች በሚሠሩት ማንኛውንም ሥራ መሪ መኖር እንዳለበት መረዳት እንችላለን፣ አንድ ሣጥን ወይም ጣውላን ለማንሣት፡- "አንተ በዚህ በኩል ያዝ፣ እኔ ደግሞ በዚያ በኩል እይዛለሁ" በማለት መመሪያ የሚሰጥ ሰው ያስፈልጋል። በማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ መሪዎች መኖር አለባቸው። በትምህርት ቤትም ሆነ በቤተክርስቲያን ውስጥ የመሪዎች መኖር አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ለምንድነው እንዲህ መሆን ያስፈለገው? የሚሰጠውስ ምክንያት ምንድነው?*

1/ ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

*ሀ/ ሰዎችን በቡድን ለማደራጀት    ሐ/ ዓላማን ለመፈፀም*

ለ/ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሌሎችን እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ

## መሪነት ሲብራራ

### ዓላማ 1፡- መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ማብራሪያ ለመስጠት

መሪ የሚያስፈልገው አንድን ዓላማ ለመፈጸም ወይም አንድን ተግባር በሚገባ ለማከናወን እንዲያስችል ነው። ክርስቲያን መሪ የሚኖረውም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓላማ ስላለው ዓላማውን እግቡ ለማድረስ መንፈሳዊ መሪነት መኖር አለበት። እግዚአብሔር በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ ፍቅሩንና ምሕረቱን ለመግለጽ ስለሚፈልግ ይህን ዓላማውን እግቡ ለማድረስ መንፈሳዊ መሪዎችን መምረጥና ማዘጋጀት ይኖርበታል።

እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲወዱትና እንዲያመልኩትም ስለሚፈልግ ራሱን የቻለ እቅድ አለው። ስለ እግዚአብሔር እቅድ ስንናገር ዓላማውን ስለሚፈጽምበት መንገድ መናገራችን ነው። የእግዚብሔር ፈቃድ በድንገት ወይም በአጋጣሚ የሚፈጸም ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእቅዱ መሠረት ዓላማው ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚፈጽመውም አስቀድሞ ያውቃል።

በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ልንገነዘበው የሚገባን ሌላው ጉዳይ ደግሞ ሥራውን የሚያከናውነው በመንፈስ ቅዱስ በሚመሩና ከእርሱም ኃይልን በተቀበሉ ሰዎች መሆኑ ነው። አላማውን ለመፈጸም እግዚአብሔር ሰዎችን ይመርጣል። በተለያዩ የአገልግሎት መስኮችም ያሰማራቸዋል።

2/ በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በመጻፍ አብረው የሚሄዱትን አመልክት።

1/ መሪው እቅድ አለው 2/ መሪው እቅድ የለውም 3/ መሪው ዓላማው

--- ሀ/ አንድ መሪ ሰዎች ወደቤተክርስቲያን እንዲመጡ ያነሣሣል።

---- ለ/ አንድ መሪ በሚቀጥለው ሳምንት 200 ሰዎች በቤተክርስቲያናችን ስብሰባ

እንዲካፈሉ ማድረግ ነው ይላል፡፡

------ሐ/ በዚህ ሳምንት መኅብኘት ያለባቸውን ሰዎች ዝርዝር ለእያንዳንዱ አገልጋይ ይሰጣል፡፡

3/ ይህን ዓረፍተ ነገር ትክክል የሚያደርገውን ፊደሉን በማክበብ አመልክት፡፡ እግዚአብሔር እቅድ አለው ስንል፡-

ሀ/ ሁልጊዜ እግዚአብሔር በአንድ ዓይነት መንገድ ይሠራል ማለት ነው፡፡

ለ/ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የራሱ መንገድ አለው ማለት ነው፡፡

ሐ/ እግዚአብሔር የሚሰራው ያለሰዎች ነው ማለታችን ነው፡፡

መ/ እግዚአብሔር የሚሰራውን አስቀድሞ ያውቃል ማለታችን ነው፡፡

## የመሪነት ማስረጃዎች

### ዓላማ 2፡- መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተካተተ ለመሆኑ ማስረጃዎችን ለማቅረብ

መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ሥፍራ ያለው መሆኑ የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንን መረዳት የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስንና እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት ሰናጠና ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደረጉትን ነገሮች ስንመለከት እግዚአብሔር በየትኛውም ጊዜ ለተለያዩ ሰዎች አንድ ዓይነት የሥራ እቅድን እንዳልሰጠ ለመረዳት እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር በግለሰቦች አማካኝነት ይሠራል፣ እነርሱም ደግሞ ከጌታ የተቀበሉትን ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎችን ያሳትፋሉ፡፡ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎችን ያሳትፋሉ፡፡ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ኃላፊነትን በመስጠት እነዚህ ሰዎች መሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን በተግባር ለማዋል የሚመሩዋቸውን ሰዎች በቡድን በማደራጀት መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተካተተ የታሪክ ማስረጃ መሆኑ ያመለክታሉ፡፡

በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ በጽሑፍ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ እቅዱን ለመፈጸም ለመሪነት መመረጣቸውን እግዚአብሔር ለግለሰቦቹ

በሚገልጥላቸው ወቅት ዝርዝር መመሪያዎቹን ጭምር ይሰጣቸዋል። ስለዚህም መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ያላቸው ሥፍራ በሚሰጣቸው መመሪያ ይረጋጣል ማለት ነው።

## የአገልግሎት ስጦታዎች

በኤፌሶን 4፣11-16 እና በሮሜ 12:6-8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚነግረን በቤተክርስቲያን አንዳንዶቹ የመሪነት ሥፍራዎችን እንዲይዙ እግዚአብሔር ሰዎችን ሰጥቷል፣ እነዚህም ሰዎች፡- ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ናቸው። የእነዚህ ሰዎች የሥራ ድርሻ ደግሞ መሪነት መሆኑ አያጠያይቅም። ከዚህም በተጨማሪ ለመሪነት የሚያበቁ እንደ አስተዳደርና እርዳታን የመሳሰሉ ስጦታዎችን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን አበርክቷል። እነዚህን ስጦታዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የአገልግሎት ስጦታዎች በማለት ይጠሯቸዋል። መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ሥፍራ ያላቸው ስለመሆኑ እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ራሳቸው ማስረጃ ናቸው።

## የመሪነት መስፈርቶችና ኃላፊነቶች

የመንፈሳዊ መሪዎችን መስፈርትና ኃላፊነትን አስመልክቶ ያሉት ማስረጃዎች በብሉይ ኪዳን ለካህናትና ለነገሥታት የተሰጡ መመሪያዎች ናቸው፣ በአዲስ ኪዳንም መሪዎችን በሚመለከት ለመሪነት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በግልጽ ተቀምጠዋል። በመሪነት ደረጃ ያሉ ሰዎች በመንፈሳዊ፣ በሞራላዊና በአእምሮአዊ ደረጃ ብቃት ያላቸው ሆነው መገኘት እንደሚገባቸው ሐዋርያት ልዩ ትኩረት ሰጥተውታል።

ስለ እግዚአብሔር ጥሪ፣ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና መሪዎችን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መስፈርቶች በዚህ ክፍለ ትምህርት በቂ ግንዛቤ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን በመጠቀስ መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ መካተቱን ማሳየት ብቻ በቂ

አይሆንም፡፡ በቤተክርስቲያን በኩል መሪዎችን በመጥራትና በመምራት ዓላማውን በዚህ ምድር ላይ ለመፈጸም በመረጣቸው ሰዎች በኩል እንዴት እንደሚሠራ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ፣ የቤተክርስቲያንና የሌሎችም ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ሕልውና እግዚአብሔር በመሪዎች በኩል እንደ ሠራ ግልጽ የሆነ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል፡፡

4/ ከዚህ በታች አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተሰጥተዋል፣ በጥንቃቄ አንብባቸው፡፡ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት ከፈለግህም ጠቅላላውን ምዕራፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብብ፡፡ ከዚያም በኋላ እያንዳንዱን ጥቅስ ቀጥሎ ካሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዝ፡፡

| | |
|---|---|
| 1/ ታሪካዊ ማስረጃ | 3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያዎች |
| 2/ የአገልግሎት ስጦታዎች | 4/ መስፈርቶችና ኃላፊነቶች |

---ሀ/ ሂዱና አሕዛብን ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ማቴ 28፣19

---ለ/ ሙሴም ከእሥራኤል ሁሉ አዋቂዎችን መረጠ፡፡ በሕዝቡም ላይ ሾማቸው ዘዳ 18፣25፡፡

---ሐ/ ዲያቆናት ልጆቻቸውንና_____________እንደሚገባ ያሳድጉ 1ኛ ጢሞ 3፣12

---መ/ እርሱም አንዳንዶች ሐዋርያት፣ ሌሎችም ነቢያት፣ ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ ኤፌ 4፣11

----ሠ/ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአሔርን መንጋ ጠብቁ 1ኛ ጴጥ 5፣2

---ረ/ ኢያሱም ጽኑአን ሃያላን ሰዎችን መረጠ---- ሰደዳቸው ኢያሱ 8፣3

## የዮሴፍ ምሳሌነት

## ዓላማ 3፡- ከዮሴፍ የሕይወት ልምምድ የመሪነትን መመሪያዎች ለይቶ ለማወቅ

የማሕበረ ምዕመናን የአምልኮ ስፍራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ብዙውን ጊዜ መሪዎች የለፉባትና የደከሙባት ውጤት ናት፡፡ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት ሲንቀሳቀሱ ነፍሳት ይድናሉ፣ ክርስቲያኖችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ፡፡ ይህም አገልግሎት እየዳበረና እየቀጠለ ሲሄድ፣ የመሪነትን አገልግሎት እያሰፋው ይሄዳል፡፡ የበለጠ አመራርን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

የመሪነትን ኃላፊነት የሚቀበል ሰው አስተሳሰቡ ለዚያ ስፍራ መሪ ሲሆን የበቃው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነና ጸሎት እንደሚያስፈልገውም ሊገነዘብ ይገባል። በጥንቃቄ እቅድ በማውጣት ግልጽ መመሪያ ለሌሎች የመስጠት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት የሚጥረው የጌታ ሥራ እየተሰፋፋ እንዲሄድ የማድረግ ፍላጎት ስለሚያድርበት ነው። ይህን ሁሉ ስንመለከት በውስጣችን የሚያሳድረው ጥያቄ፣ አንድ ክርስቲያን የመሪነትን ኃላፊነት መቀበል ያለበት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው? የሚል ይሆናል።

መሪነትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ስንመረምር ለጥያቄአችን ተገቢውን ምላሽ እናገኛለን። ይህንንም በዝርዝርና በተሟላ መልኩ የምናገኘው ከዮሴፍ ሕይወት ታሪክ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ታሪኩ ከታሪካዊ እውነታ በላይ አድርጎ ይህን ያቆየልን ስለ ሰብአዊ ባሕርይ ስለ መሪነት ምሳሌና ትምህርት እንዲሆነን ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርታችን በምሳሌት የምንከተለው በዚህ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ብታነበው አይከፋም። ሙሉውን ታሪክ የምታገኘው በዘፍ 39-48 ላይ ሲሆን፣ የጥናታችን ዋና ትኩረት ግን ምዕ 37፣ 39-42፣ 41፣1-25፣ 43፣1-15፣ 24-31፣ 45፣1-15 ላይ ይሆናል።

ቀጥሎ ደግሞ ታሪኩን እጥር ባለ መልኩ በመመልከት የዮሴፍን ባህርይ እናያለን። ዮሴፍ ምን አይነት ሰው ነበር? ለሚለው ጥያቄም ለራስህ መልስ ትሰጣለህ። ለዚህም እንዲረዳን ሦስት ዓይነት ባሕርይ እንመለከታለን። እነርሱም፦ የግለሰቡ ሕይወት ብቃት፣ ሀሳብ፣ ስሜትና ሥራ ናቸው። የአንድ መሪ ስኬት ከነዚህ ሦስት ነገሮች ጋር ይያያዛል።

ስለ መሪነት የተጻፉ አንዳንድ መጻሕፍትን ስታነብ የግለሰቡ ሕይወት ብቃት የመሪነት ተፈጥሮ፣ የመራው ሀሳብና ስሜት የመሪነት ዝንባሌ የመሪው የስራ እንቅስቃሴ ደግሞ የመሪነት ጸባይ በሚሰኝ መልክ መቅረባቸውን

ትመለከታለህ። እዚህ ላይ ግን ሁሉንም እንዲያካትትልን ባሕርይ በሚለው ቃል ነው የምንጠቀመው። ሆኖም እነዚህን አገላለፆች ማወቁ ስለሚጠቅምህ በዚህ ትምህርት ውስጥ አልፎ አልፎ እናነሳቸዋለን።

5/ ተፈጥሮን፣ ዝንባሌንና ፀባይን በሚገባ ለመረዳት እንዲቻል ስለ አንድ መንፈሳዊ መሪ የተነገሩትን ዐረፍተ ነገሮች ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስፈር አብሮ የሚሄደውን አመልከት። 1/ጸባይ 2/ዝንባሌ 3/ ባሕርይ

---- ሀ/ በድሩ ፈገግ እያለ በልበ ሙሉነት ወደፊት ሔደ።

-----ለ/ በድሩ መልካም መሪ እንደሚሆን እምነት አለው።

----ሐ/ በድሩ እውነተኛ ክርስቲያን ነው።

-----መ/ በድሩ በራሱ የሚተማመን ሰው ነው።

-----ሠ/ በድሩ ግልጽ መመሪያ ሰጠ።

## ዮሴፍ በባርነት

ዮሴፍ ያየውን ሕልም በነገራቸው ጊዜ *"ታዲያ እኛ ላይ መሪና አለቃ ልትሆን ታስባለህ?"* በማለት ነበር ወንድሞቹ ያንጓጠጡት። ታላቅ መሪ እንደሚሆን በሕልሙ ቢያይም፣ ወንድሞቹ ግን የነበራቸው አስተሳሰብ እንደሌሎች ብዙ ሰዎች ሁሉ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበር።
የመሪነት ዓላማው የተወሰኑ ሰዎች በሌሎች ላይ የመሰልጠን መብት እንደሚሰጣቸው አድርገው ነበር ያሰቡት።

እግዚአብሔር ስለ መሪነት ያለው ዓላማ ግን እንደዚህ ዓይነት እንዳልነበረ ከዮሴፍ ሕይወት ለመረዳት እንችላለን። ምናልባት ዮሴፍ ሕልሙን ለወንድሞቹ ሲነግራቸው በልቡ ትዕቢት ተሰምቶታል ብለን እናስብ ይሆናል። ሕይወቱን ስንመለከት ግን የምንረዳው ዮሴፍ የሚኩራራና ሌሎችን የሚጫን ዓይነት ሰው እንዳልነበረ ነው። ምናልባትም ከመገረምና ከመደነቅ የተነሣ ሊሆን ይችላል ሕልሙን ለቤተሰቡ የነገራቸው። ለአንድ ዓይነት ዓላማ እግዚአብሔር እንደጠራው ተረድቷል። ይህን ለማለት የምንችለው ወደ መሪነት የመጣው ለራሱ ክብር ላይሆን፣ በእግዚአብሔር

እቅድ መሠረትና ዓላማውን ለመፈጸም እንደሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ቃል መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ምናልባትም ዮሴፍ በወጣትነት ዘመኑ ይህን ላይረዳው ይችል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደሚመራው እርግጠኛ መሆኑን ግን መረዳት ይቻላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ***እግዚአብሔርም ከዮሴፍ ጋር ነበር*** በማለት ይናገራል፡፡ ዮሴፍ ይህን በሚገባ ተገንዝቧል፡፣ ድርጊቱን ስንመለከት በእግዚአብሔር ምህረት ላይ ያለውን መታመን ለመረዳት እንችላለን፡፡

6/ ከዮሴፍ ሕይወት ልምምድ የእግዚአብሔርን የአሠራር መንገድ ታያለህን? ለምንድነው አግዚአብሔር መሪዎችን የሚመርጠው? መልስህን በተሰጠህ ሥፍራ አስፍር፡፡

ቀናተኞቹ ወንድሞቹ ዮሴፍን ለባርነት ሸጡት፣፡ ወደ ግብጽ ተወስዶም አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ገዛው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ መሪ ሆነ፣፡ ይህም የመካከለኛ አመራር አሰራር ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ዮሴፍ የተገዛ ባሪያ በመሆኑ የጌታውን ትዕዛዝ መፈጸም ነበረበት፣፡ በሌላ በኩል ደግሞ የዮሴፍ ጌታ እንደሚገባ ሥራውን ለማከናወን ረዳት ስላስፈለገው መካከለኛ መሪ በመሆን ኃላፊነቱን እንዲሸከም ዮሴፍን መረጠው፡፡ ዮሴፍ የጌታውን ቤተሰብና ንብረት የማስተዳድር ኃላፊነት ተሰጠው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ***እግዚአብሔር የዮሴፍን ሥራ ሁሉ አከናወነለት*** ይላል፣ ይህንንም የዮሴፍ ጌታ አስተውሏል፡፡ የስኬቱና የመከናወኑ ምክንያት እግዚአብሔር መሆኑን ግልጽ አድርጓል፡፡ ***እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር*** ሲባል ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊውን ብርታት ሰጠው ማለት ነው እንጂ ሥራው ቀላል ነበር ማለት አይደለም፡፡ ምንም ዓይነት ችግር ወይም ፈተና እንዳይገጥመው አደረገ ማለትም አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ችግሮቹን የሚወጣበት ጥበብ፣ ድፍረትና እምነት ሰጠው ማለት ነው፡፡

ትልቁ ፈተና የተጀመረው የጌታው ሚስት ከእርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት እንዲያደርግ በተፈታተነችው ጊዜ ነበር፡፡ ዮሴፍ ግን *“ሥልጣኔን መከታ በማድረግ እንዲህ ያለውን ነውር አላደርግም፣ ጌታዬ የጣለብኝን እምነት አላጓድልም፡፡ በባረከኝ እግዚአብሔር ላይ አላምጽም”* በማለት ፈቃዷን አልፈጸመም፡፡ ዮሴፍ ጌታውን የሚያከብርና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ የሚገዛ ሰው እንደነበር በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሴትየዋ ግን ዘወትር ትንዘንዘው ነበር፡፡ ፈቃዷን ባለመፈጸሙም ዮሴፍ ላይ ተቆጣች፣: በመጨረሻም የሐሰት ምክንያት ፈጥራ ወህኒ እንዲገባ አደረገች፡፡

7/ ምንም እንኳ አንድ ሰው በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ቢሆንም፣ የተዋጣለት መሪ መሆን እንደሚችል ከዮሴፍ ታሪክ መመልከት ይቻላል፡፡ ዮሴፍ ነገሩ ሁሉ እንዲከናወን ዋና ምክንያት የሆኑትን ሁለት ነገሮች ፊደሉን በማክበብ አመልክት፡፡
ሀ/ ከበታቹ ያሉት ሰዎች ሙሉ በሙሉ እንዲታዘዙለት ይፈልግ ነበር፡፡
ለ/ ከእርሱ በላይ ያለውን ባለሥልጣን ያከብር ነበር፡፡
ሐ/ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ነበር የሚንቀሳቀሰው፡፡
መ/ እግዚአብሔር ሥራውን ቀላል እንደሚያደርግለት ያምን ነበር፡፡

## ዮሴፍ በእስር ቤት

በወህኒ በነበረበት ጊዜ መሪ እንደሚሆን ያለመው ሕልም ጨርሶ እንደማይፈጸም ሳያስብ አልቀረም፡፡ የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል፣ ከበታቹ ያሉት ግን በእርሱ ላይ ተነስተውበታል፡፡ *“ሰዎች እንደሁ እንደዚህ ናቸው፣ ማመን አይቻልም፣ ታዲያ ምን ዋጋ አለው”* አለማለቱ ራሱ ዮሴፍ እውነተኛ መሪ ለመሆኑ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው፡፡

ዮሴፍ በጣም ብልህ ሰው በመሆኑ ሰዎች ያደረጉበት ትክክል እንዳልነበረ አውቆ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ አደረገ፡፡ በተለያዩ የሕይወት ደረጃ ካሉ ሰዎችም ጋር መልካም ግንኙነት ነበረው፡፡ በእሥር ቤት ሆኖ እንኳ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሕልም በዮሴፍ ሕይወት ተጽእኖ ነበረው፡፡ እንዲያውም የመሪነት ብቃቱ እንደገና ይበልጥ ጎልቶ በዚያ ስለታየ ምንም እንኳ በዝርዝር ባይገልጽልንም መጽሐፍ ቅዱስ

*“እግዚአብሐር ከዮሴፍ ጋር ነበር፣ ሥራውንም ሁሉ አከናወነለት፣ የወህኒ ቤቱ ኃላፊ በሌሎች እሥረኞችና በወህኒ ቤቱ ላይ ኃላፊ አደረገው”* በማለት ይነግረናል።

እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር መሆኑን የወህኒ ቤቱ ኃላፊ እንዴት አወቀ? አንድ ሰው በወህኒ ውስጥ ሆኖ ከእግዚአብሔር የመሪነት ችሎታ የተሰጠው መሆኑን እንዴት ማሳየት የሚችል ይመስልሃል? የወህኒ ኃላፊው ያየው ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች በአእምሮህ ያዛቸው። ቆየት ብለን የዮሴፍን ታሪክ ስለመሪነት ከተጻፉ ሌሎች መጻሕፍት ጋር ስናነጻጽር ዮሴፍ በሕይወቱ ያሳያቸውን አንድን መሪ ብቁ የሚያደርጉ ባሕርያትን እንመለከታለን።

የንጉሡ ምግብ ቤት ኃላፊና የጠጅ አሳላፊም ከዮሴፍ ጋር አብረው ታስረው ነበር። ኃላፊነት ስለነበረው እነዚህ ሰዎች ከዮሴፍ በታች ነበሩ። አንድ ቀን ከሌላው ጊዜ ይልቅ በጣም አዝነው እንደነበር ተረዳ። ስለዚህም ***ምነው አዝናችኋል?*** በማለት ሲጠይቃቸው የሚያስጨንቁ ሕልሞችን ማየታቸውን ነገሩት። ***“እግዚአብሔር የሕልማችሁን ትርጉም ሊገልጽልን ይችላል”*** አላቸው። ይህም ምን ያህል ከእግዚአያብሔር ጋር የተቀራረበ ሕይወት እንደነበረውና ያለውንም እምነት የሚያሳይ ነው።

እግዚአብሔር የሕልሙን ትክክለኛ ትርጉም ለዮሴፍ ገለጠለትና ትርጉሙን ነገራቸው። የጠጅ አሳላፊው ሕልም ከእሥር እንደሚፈታና ወደ ቀድሞ ሥራው እንደሚመለስ የሚያመለክት ነበር። ዮሴፍም በአጋጣሚው ለመጠቀም እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ ***“ከእስር ቤት ስትወጣ እኔንም እንዳትረሳኝ፤ ጉዳዬን እንዲያይልኝም ለንጉሱ ንገርልኝ”*** አለው።

ከሁለት ዓመት በኋላ ንጉሱ አንድ አስጨናቂ ህልም አለመ። ሕልሙም እንዲተረጉምለት ምን እንደሆነም ብዙ ሰዎችን ጠየቀ። በመጨረሻም የጠጅ አሳላፊው በእሥር ቤት በነበር ግዜ የገጠመው ትዝ ስላለው ለንጉሱ ስለ ዮሴፍ ነገረው። ዮሴፍንም ከእስር ቤት አወጡትና ሕልሙን እንዲፈታ ንጉሱ ፊት አቀረቡት። እዚህም ላይ ዮሴፍ ስለ ህልሙ ትርጉም ክብሩን ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ነው የምንመለከተው።

8/ እግዚአብሔር በነበረው እቅድ መሠረት ዮሴፍን ከእሥር ቤት ለማስወጣት በሌላ እሥረኛ ሕልም ተጠቀመ። ዮሴፍ ስለዚያ ህልም ያወቀው እንዴት ነበር? ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

ሀ/እሥረኞቹ ወደ እርሱ መጥተው ምክር እንዲቀበሉ ዮሴፍ ነገራቸው።

ለ/ ለምን እንዳዘኑ ዮሴፍ እሥረኞቹን ጠየቃቸው።

9/ ለመጨረሻው ጥያቄ የሰጠኸው መልስ ስለ ዮሴፍ ባሕርይ ምን ያመለክትሃል? ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

ሀ/ ከሰዎች ተግባቢ መሆኑን ለ/ ማንነቱን ሰዎች እንዲያውቁለት የሚፈልግ መሆኑን

## ዮሴፍ በድል አድራጊነት

ዮሴፍ ለንጉሡ ***"ሕልሙ የሚያመለክተው የረሃብ ጊዜ እንደሚመጣ ነው"*** አለው። ***"ለሰባት ዓመት ያህል በዚህች አገር በጣም ሰፊ ምርት የሚኖርበት ጊዜ ይመጣል። ከሚያስፈልገው በላይ እህል ይኖራል። ከዚህ በኋላ ደግሞ በዚህ አገር ብቻ ሳይሆን በአካባቢው አገሮች ሁሉ ሰባት የረሀብ ዓመታት ይኖራሉ። ስለዚህም በመልካሞቹ ዓመታት የሚኖረውን የተትረፈረፈ ምርት ማከማቸቱ የችጋር ዓመቶችን ያለምንም ችግር እንድታሳልፍ ይረዳሀል።"***

ንጉሡ በዮሴፍ ጥበብ በመደነቅ ***"የራስህን ሃሳብ ራስህ እንድትፈጽም ዕድል ሰጥቼሃለሁ"*** አለው። ስለዚህም ዮሴፍ ከእስር በመፈታት ከንጉሡ ቀጥሎ የዚያ አገር ባለሥልጣን ሆነ። በእቅዱ መሠረትም ትርፍ እህል በጎተራ በማከማቸት ሁሉም ነገር ልክ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት እንዲፈጸም አደረገ። የረሀቡ ጊዜ ሲመጣ የተከማቸውን እህል ለሕዝቡ በማደል ሕዝቡ ከረሃብ ችግር እንዲድን ተደረገ። ከአካባቢው አገሮችም ብዙዎቹ እህል ለመሸመት ይመጡ በነበሩ ሰዎች መካከል የዮሴፍ ዝና እየገነነ በመሄዱ በጣም የተከበረ ሰው ሆነ።

አንድ ቀን ዮሴፍ ከአካባቢው አገሮች ለሚመጡ ሰዎች እህል የመሸጡን ሥራ እየተቆጣጠረ እያለ፣ ዮሴፍ እህል ለመግዛት የመጡትን የገዛ ወንድሞቹን በዓይኑ አያቸው። የሚያማምሩ ልብሶች በመልበሱና እነርሱ ለባርነት ከሸጡት ዮሴፍ በፍጹም የተለየ በመሆኑ ወንድሞቹ ለይተው ሊያውቁት አልቻሉም። ዮሴፍ ግን ወንድሞቹ እንደሆኑ ሊያውቃቸው ችሏል። እንደ አንድ ንጉሥ ወድቀው ሰገዱለት። በመጨረሻም መሪ እንደሚሆን ያየው ሕልም በትክክል ተፈጸመ።

ዮሴፍ በሥልጣኑ እንዳልተኩራራ፣ ክፉ ያደረጉበትን ወንድሞቹንም መበቀል እንዳልፈለገ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተሰጠው ታሪኩ ለመረዳት እንችላለን። ለወንድሞቹ ትምህርት ለመስጠት ነበር አጋጣሚውን የተጠቀመበት። ይህን ያደረገውም እነርሱን መጥቀም በሚችልበት ሁኔታ በደግነት መንገድ እንጂ ታላቅነቱን በማሳየት አልነበረም። በመጨረሻም ስሜቱን ለመግለጽ አላፈረም። በደስታና ለቤተሰቡ ባለው ፍቅር አለቀሰ። ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር የተመረጠ የተዋጣለት መሪ ያደረገው ደግሞ ዮሴፍ በታላቅ ኃይልና ድል ላይ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠቀምበትና መለኮታዊ ዓላማውን የሚፈጽምበት መሣሪያ መሆኑን መገንዘቡ ነበር።

10/ እንደገና ዘፍጥረት 45፣4-13 አንብብ። አንዳንድ መሪዎች ስላለፈው ስህተታቸውና ጉድለታቸው ሰዎችን ይወቅሳሉ። ዮሴፍ ወንድሞቹን ወቀሳቸውን? በአጭሩ ግለጽ -------------------------------------------

## የመሪነት ባሕርያት

### ዓላማ 4፡- የመሪነትን ባሕርያት በመረዳት ለመዘርዘርና ምሳሌዎችን ለመስጠት

ስለ መሪነት እንደሚገባ ያጠና ማንኛውም ሰው እንደሚገነዘበው መሪዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ባሕርይ አላቸው ማለት አይቻልም። ስለዚህ ጉዳይ በመቶ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ቢኖሩም መሪነትን አስመልክቶ አንድ መጽሐፍ 339 የመሪዎች ባህርያትን በዝርዝር እንዳሰፈረ ይነገራል። አንዳንድ ጸሐፊዎች ደግሞ መሪነትን በባሕርይ በመተንተን መረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መወያየቱ ምንም ጥቅም የለውም የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ።

ተፈጥሮ፣ ዝንባሌና ባሕርያት በራሳቸው አንድን የተዋጣለትን መሪ መግለጽ እንደማይችሉ የእኛም እምነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመጠኑም ቢሆን የመሪዎችን ባሕርይ ማጥናቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ግልጽ በመሆኑ ስለ ዮሴፍ ሕይወት በማጥናት ጀምረነዋል፡፡ ተፈጥሮው /የሰውየው ማንነት/ ዝንባሌው /ስሜቱና አስተሳሰቡ/፣ ባሕሪው /የሚሰራው ሥራ/፣ በአንድነት ተጣምረው የተዋጣለት መሪ እንዳደረጉት ተመልክተናል፡፡

ለምሳሌም ያህል ዮሴፍ ብልህ እንደነበር ፈርዖን ከተናገረው ከዘፍ 41፣39 ላይ ተረድተናል፡፡ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ በሕይወቱ እቅዱን እስኪፈጽም ድረስ ታግሷልና ታጋሽ እንደነበር መመልከት አያዳግትም፡፡ ስለዚህም ብልህነትና ትዕግሥት የአንድ መሪ ባሕርያት ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ እንዲህም ስለተባለ ማንኛውም ብልህና ታጋሽ ሰው መልካም መሪ መሆን ይችላል ማለታችን አይደለም፡፡ በሕይወታችን የመሪነት ባሕርያትን ማዳበር ከፈለግን እግዚአብሔር ብልህነትንና ትዕግሥትን እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን ማለታችን ነው፡፡ ብልህና ትዕግሥተኛ ከሆንን ከመሪነት ባሕርያት ጥቂቶቹን አዳብረናል ማለታችን ነው፡፡
መሪነትን አስመልክቶ በርከት ያሉ መጻሕፍት ተጽፈዋል፡፣ ከእነዚህ ታዋቂ ከሆኑ መጽሕፍት ካገኘናቸው የመሪነት ባሕርያት ጥቂቶቹ እነሆ፡-
1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት ወይም ለሌሎች ማሰብ
2/ እግብ ላይ መድረስና ግብን መምታት
3/ ለሥራው ወይም ለኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት
4/ ስሜታዊ መረጋጋት ወይም ወላዋይ አለመሆን
5/ በቡድን መሥራት 6/ ሥልጣንን ለሌሎች ማካፈል
6/ቃልና ድርጊትን ማጣመርና እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት ነው፡፡

እነዚህን ባሕርያት አንድ በአንድ ስንመረምር፣ ስለመሪነት በተጻፉ ሌሎች መጻህፍት ብቻ ሳይሆን በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳ የአንድ መልካም ክርስትያን ባሕርያት ሆነው መቅረባቸውን እንመለከታለን፡፡ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ የሚከተሉትን ባሕርያትንም ያካትታል፡፡

1/ የእግዚአብሔር ጥሪ ወይም ተልእኮ

2/ የክርስቶስን ፍቅር አስተላላፊ አሸንዳ መሆንን መገንዘብ

3/ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መደገፍ

4/ በመንፈሳዊ ሕይወት ለሌሎች አርአያ ሆኖ መኖር

11/ እነዚህን ዝርዝሮች እንደገና አንብብ፣፡ ከዚያ በኋላ በቃልህ በጽሑፍ አስፍር፡፡ በጸሎትና በጾም ጊዜ ሁሉ በልብህ አሰላስላቸው፣ የሥራህ ሁሉ መመዘኛም ይሁኑ፣ ይህም መልካም መሪ ለመሆን ይረዳሀል፡፡

አሁን ደግሞ አብዛኛዎቹ ምሑራን በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን ሰባት የመሪነት ባሕርያት እንመለከታለን፡፡ ዋናው ዓላማችን አንድ መሪ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር ምላሽ ለመስጠት ሲሆን፣ ከተዋጣለት መሪ ባሕርያት ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦችንም በሚቀጥሉት ክፍለ ትምህርቶች በስፋት በመመልከት በቂ ግንዛቤ ለማግኘት እንሞክራለን፡፡

**1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት**

አንድ መሪ ከራሱ እይታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ከሌሎችም ሰዎች አንጻር ያያል፣ የሌሎችን ስሜት ለመረዳት ይሞክራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ***"ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው"*** ይላል /ሉቃስ 6፣31/ ፡፡ ይህም ወርቃማው ትእዛዝ በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊም ***"ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፣ የተጨቆኑትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ"*** ይላል /ዕብ 3፡3/፡፡ አዛኞችና ሩህሩሆች እንድንሆን የሌሎችንም ሸክም እንድንካፈል ተነግሮናል /1ኛ ጴጥ 3፡8፣ ገላ 6፣2/፡፡ የሌሎችን ስሜት መረዳትና ለሌሎች ማሰብ ለክርስቲያናዊ ሥራ እና አገልግሎት በጣም አስፈላጊ ሲሆን፣ ይልቁንም ደግሞ ለአንድ መንፈሳዊ መሪ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2. ግብ ላይ መድረስ

አንድ መሪ ዓላማና ግብ ይኖረዋል፣፡ ዓላማ ላይ ለመድረስና ግቡን ለመምታት በርትቶ መሥራት አለበት፡፡ መንፈሳዊ መሪ ለራሱና የእግዚአብሔርን ዓላማ በመፈጸም ረገድ አብረውት ለሚሠሩ ሁሉ ዓላማና ግቡን ቁጭ አድርጎ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ሲገልጥ ***"ሽልማቴን ለማግኘት በፊቴ ወዳለው ግብ እሮጣለሁ"*** ብሎ በገጽ 15 ይናገራል፡፡ ለፊልጵስዩስ በጻፋቸው መልእክቶቹ ሁሉ ዓላማውን እግቡ የማድረስ ሀሳብና ፍላጎት እንዳለው በግልጽ ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔርን "ዘላለማዊ ዓላማ" ለመፈጸም "ያለውን ዓላማ"፣ ምክንያትና ፍላጎት በተደጋጋሚ ይገልጻል፣ ኤፌ 3፣10-11፣ እና 2ኛ ጢሞ 2፣10 ለምሳሌ ያህል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3. ብቁ ሆኖ መገኘት

አንድ መንፈሳዊ መሪ ለሥራውና ለኃላፊነቱ ብቁ ሆኖ መገኘት ሥራውን ጥራት ባለው መንገድ በማከናወንና ዓላማውን እግብ ለማድረስ እንዲችል ይረዳዋል፡፡ ሌሎችንም በሥራቸው ለመርዳት የሚያስችለውን መንገድ በመቀየስ ከእርሱ ጋር አብረው ተግተው እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ራሱንም ሆነ ሌሎችን የሚመዝንበትና የሚለካበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መመሪያዎች በሚገባ በማወቅና በመከተል መልካም አርአያ በመሆን ኃላፊነቱን በትጋት በመወጣት ሌሎቹም እንደእርሱ ኃላፊነታቸውን በትጋት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ዘጸ 35፣36፣ ምሳ 12፣ 27፣22፣ 29:31፣10-30፣ 2ኛ ጢሞ 2: ያዕ2፣ 14-16፣2 ጴጥ 1፣5-10 ተመልከት፡፡

## 4. የስሜት እርጋታ

የስሜት መረጋጋት ስንል ወላዋይ አለመሆን ማለታችን ነው፡፡ አንድ መንፈሳዊ መሪ አስተሳሰቡን መጠበቅ አለበት፡፡ ለሚያደርገው ሁሉ ምክንያት ያለውና በራሱ የሚተማመን ረጋ ያለ ሰው መሆኑ ወሳኝ ነው፡፡ በቀላሉ የማይናደድና የራሱ ፈቃድን ብቻ ተከትሎ የሚሄድ እንደዚሁም በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ሰው መሆን

የለበትም፡፡ ሁኔታዎች ሁሉ እርሱ እንደጠበቃቸው ሳይሆኑ ሲቀሩና የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሙት ሰላማዊ በሆነና ረጋ ባለ መንፈስ ለገጠሙት ችግሮች መፍትሔ የሚፈልግ ሰው መሆን አለበት፡፡ ዳዊት በመዝ 27፡14 ላይ ይህን በሚገባ የሚገልጸው በእግዚአብሔር እንደሚታመን ሰው ሆኖ ***"በርታ ልብህም ይጽና"*** በማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኤፌ 4፡31፣ በ2ኛ ጢሞ 4፡5 በ1ኛ ጴጥ 4፡7 ላይ ስለዚሁ የተሰጠውን ምክርና መመሪያ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

### 5. በቡድን መስራት

አንድ መሪ ራሱ የቡድኑ አካል ወይም አባል እንደሆነ ጠንካራ እምነት ሲኖረው፣ ከሌሎች ጋር የሥራ ኃላፊነትን በመጋራት አብሮ መሥራት ደስ ያሰኘዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ አሠራር በ1ኛ ቆሮ 12ና በኤፌ 4 ላይ አካል ምሳሌነት የተገለጸ ሲሆን፣ አንድ መንፈሳዊ መሪ ማሰብ ያለበት እያንዳንዱ የአካል ክፍል ተደጋግፎና ተሳስቦ የመሥራት ኃላፊነት እንዳለበት ሊሆን ይገባል(ኤፌ 4፣16)፡፡ እያንዳንዱ የአካል ክፍል ተደጋጋፊ በመሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት ሲሠሩ ውጤታማ የሆኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ፡፡ ስለዚህም መሪው ከእንደዚህ ዓይነቱ ከሌሎች ተነጥሎ ምንም ውጤታማ መሆን ስለማይችል ከእነዚህ አንዱ መሆኑን አስቀድሞ መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

### 6. ሥልጣንን ለሌሎች የማካፈል ችሎታ

አንድ መሪ በመልካም ሁኔታ ከሌሎች ጋር ሲሠራ፣ እንደ መካከለኛ መሪ ሆኖ ሥፍራውን ሲቀበል ነው፡፡ ሌሎች በታማኝነትና በአክብሮት የሚከተሉት ረዳት እንዲሆኑትም የሚተማመንባቸውን ረዳት እንዲሆኑት ሌሎችን በመሪነት ደረጃ ቢመርጥም፤ የስራው አይነት ከበላይ ሆኖ እንዲቆጣጠራቸው ሊያስገድደው ይችላል፡፡ ይህ አሠራር ከቡድን አሠራር ጋር በጣም የተያያዘ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ትህትና፣ መተማመንና መከባበር ናቸው፡፡ እውነተኛ መሪ ለሌሎች ከፍተኛ አክብሮት ያለው ሰው መሆን አለበት፡፡ የእግዚአብሔር አሠራር ከፍጥረቱ ሁሉ ክቡር በሆነው በሰው ልጅ አማካይነት መሥራት እንደሆነ ለመሪነት የተጠራው ሰው በሚገባ በመረዳት

የስጦታዎቹና የጥሪው ዋና ዓላማ በእርስ በርስ መከባበር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም አስቀድሞ ሊከበር የሚገባው እግዚአብሔር ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 5፡21 ላይ ስለዚሁ ምክር ሲሰጥ፡- *"እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ"* ጳውሎስ ለሥራ ባልደረቦቹና ረዳቶቹ ያለውን አክብሮት ደጋግሞ ይገልጣል፣ ይህንንም የሚያደርገው ለክርስቲያን መሪዎች ምሳሌ ለመሆን ነው፡፡ ጳውሎስ ለሌሎች ያለውን አክብሮት ከገለጸባቸው ክፍሎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፊል 4፣1-3 ፡ ቆላ 4፣7-14 እና 1ኛ ተሰ 1፡2-4፡፡

## 7. ቃሉን በተግባር በመተርጎም እምነት የሚጣልበት

አንድ መሪ ቃሉን የሚጠብቅና ሌሎችም የሚታመኑበት ዓይነት ሊሆን ይገባል፡፡ ከሌሎች የሚጠብቀውን በግልጽነትና በቅንነት በማስተላለፍ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግም እገዛ ያደርጋል፡፡ በአንድ ወቅት በስሜት ተነሳስቶ የተናገረውን በሌላ ጊዜ የሚዘነጋ ወይም ለሌሎች አስቀድሞ ሳያስታውቅ ሃሳቡን የሚለውጥ ዓይነት ሰው መሆን የለበትም፡፡ ቃሉን ይጠብቃል፣ ለሌሎች ለሰጠው መመሪያም እርሱ ራሱ ታዛዥ መሆኑንም በተግባር ያሳያል፡፡ ቃልና ሥራን ማጣመር እንዲሁም እምነት የሚጣልበት መሪ ሆኖ መገኘት ለክርስቲያናዊ አገልግሎት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ኢየሱስ ራሱ ሲገልጽ፡- ***"ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኃላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም"*** ይላል፡፡ ጳውሎስም ይህንኑ በማጽናት በ1ኛ ቆር15፣58 ላይ፡- ***"የምትደላደሉ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታም ሥራ የሚበዛላችሁ ሁኑ"*** በማለት ይናገራል፡፡ በተጨማሪም በገላ 5፡1ና በኤፌ 4፡14 ይህንኑ አስመልክቶ የተናገረውን ተመልከት፡፡

12/ እዚህ ላይ ስለ ዮሴፍ ዝንባሌና ባሕርይ ሰባት ነጥቦች ተሰጥተዋል፡፡ እያንዳንዳቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከላይ ከዘረዘርናቸው ባሕርያት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ትክክለኛውን ባሕርይ የሚገልጸውን ቁጥሩን ከዐረፍተ ነገሮቹ ፊት በማስቀመጥ አመልክት፡፡

----ሀ/ ዮሴፍ ለፈርዖን፣ ሰባት ዓመት የሚበቃ እህል እናጠራቅማለን አለው፡፡

---ለ/ ምንም እንኳ ወይን ጠጅ አሳላፊው ቢረሳውም ዮሴፍ አልተናደደም፡፡

----ሐ/ ሥጋ ዘመዶቹን አልረሳቸውም፣ ለሕዝቡ መልካም ነገር ማድረግ እንዳለበትም ያውቃል፡

---መ/ ምንም እንኳ ያለ በደሉ ግፍ ቢደርስበትም በእግዚአብሔር የሚተማመንና በታማኝነትም ሥራውን ይሰራ ነበር፣

---ሠ/ ዮሴፍ ወንድሞቹ እንደተጸጸቱ ስላወቀ ሊያጽናናቸው ሞከረ፣

---ረ/ አሳዳሪ ጌታውና የወህኒው ኃላፊ ዮሴፍ ነገሮችን በትክክል ያደርግ እንደነበር አዩ፡

----ሰ/ ለአሳዳሪ ጌታው፣ ለወህኒ ኃላፊና ለንጉሡ ታዛዥና አክባሪ ነበር፡

ስለ አንድ መሪ ተፈጥሮ፣ ዝንባሌና ጸባይ ለመረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ የዮሴፍን ታሪክ በሚገባ ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ምሁራን የመሪዎች ባሕርያትን በተመለከተ ያሰባሰቧቸውን ዝርዝር መሠረት በማድረግ የአንድ መንፈሳዊ መሪ ባሕርይና ከዮሴፍ ሕይወት ሊከተለው የሚገባ ምሳሌ ምን መሆን እንዳለበት በቂ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

ከጌታና ከመጋቢው በታች ሆኖ የሚሰራ በመሠልጠን ላይ መካከለኛ መሪ በትሕትና ላይ የተመሰረተ ዝንባሌ ሊኖረው ይገባል፡፡ ከወንድሞቹም ሆነ ከሌሎች ወጣቶች የላቀ ደረጃ ስላገኘ መኩራራት የለበትም ፡፡ እንደ ዮሴፍ አንድ እውነተኛ መሪ ከበላዩም ሆነ ከበታች ያሉትን ያከብራል፡፡ መልካም መሪ ለሌሎች ከሚሰጠው መመሪያ የበለጠ ያደርጋል፡፡ ከሌሎች ጋር ሆኖም ይሠራል፡፡ የሌሎችን ጥፋት ይቅር ይላል፡፡ በተለያየ ምክንያት ቢያሳዝኑትም ሰዎችን ይወዳል፡፡ አንድ ቀን የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡም ይጠብቃል፡፡ ዮሴፍ ለወንድሞቹ እንዳደረገው ሁሉ የጌታን ፈቃድ ለመፈጸም እንዲችሉ ወደ መንፈሳዊነት ይመራቸዋል፡፡

## የሙከራ ፈተና

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ነው የምትለውን ፊደል ክበበው፡

1/ "መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ" የሚገልጸው፡-

ሀ/ በመንፈሳውያን ፍጥረቶች አማካኝነት ዓላማውን ይፈጽማል፡፡

ለ/ ዓላማውን የሚፈጽምበት የራሱ ልዩ መንገድ አለው፡፡

ሐ/ ፈቃዱን ለመፈጸም በሰዎች መጠቀም ሞኝነት እንደሆነ ያውቃል፡፡

2/ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ በጣም አስፈላጊው ክፍል ሥራው

ሀ/ በቅኖችና መልካምን ለማድረግ ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች መሰራቱ ነው

ለ/ ዓላማውን ለመፈጸም ኃይልና ማስተዋል ባላቸው መላእክት መጠቀሙ

ሐ/ ሥራውን እንዲሰሩለት በሚያስገድዳቸው ሰዎች መጠቀሙ ነው

3/ ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት የሚያሳየው፡-

ሀ/ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ እርሱም ዓላማውን የሚለውጥ መሆኑን

ለ/ የገዛ ዓላማውና አሠራር መንገዱ እሥረኛ መሆኑ

ሐ/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስተማማኝ በሆነ መንገድ መንቀሳቀሱን

4/ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ የተካተተ ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡ ማስረጃ ሊሆን የማይችል የትኛው ነው?

ሀ/ መሪነትን አስመልክቶ በመጽሐፍ የተዘረዘሩት መስፈርቶች፣ ኃላፊነቶች

ለ/ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ቀጥተኛ ጥሪና መመሪያዎች

ሐ/ የማሕበረሰቡ ፍላጎት መሪዎች እንደሚያስፈልጉ መግለጹ

5/ በመንፈሳዊ መሪነት ውስጥ የመካከለኝነት አመራር በጣም መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የመካከለኝነት አመራር ስንል፡-

ሀ/ መሪዎች ጌታን ብቻ ይከተላሉ፡፡

ለ/ ሌሎች መሪዎችን ይከተላሉ፣ ስለዚህም ሁሉም የጌታ ተከታዮች ናቸው፡፡

ሐ/ የራሳቸውን ፍላጎትና ጌታን ይከተላሉ፡፡

6/ በዚያ የመንግሥት ባለሥልጣን ቤት በሚያገለግልበት ወቅት ከዮሴፍ ሕይወት የተመለከተናቸው ሁለት የመሪነት ባሕርያት፡-

ሀ/ ባለሥልጣንን ማክበርና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት፡፡

ለ/ ሁሉን ለማስደሰትና በሁሉም ታዋቂ የመሆን ፍላጎት ነበረው፡፡

ሐ/ በሥልጣኑ ያለአግባብ ይጠቀም ነበር።

7/ ዮሴፍ በእሥር ቤት ሳለ በሌሎች የተሳካላቸው መሪዎች የሚታዩ ባሕርያት ታይተውበታል። በእግዚአብሔር ላይ የማያወላውል እምነት፣ በአገልግሎት ታማኝነትና፡-

ሀ/ ነገሮች ሁሉ ወደ መልካምነት እንደሚለወጡ የነበረው ተስፋ

ለ/ ሁኔታዎች ላልሰመሩላቸው ሰዎች መራራት

ሐ/ ሰዎችን መቅረብና ለሌሎች ማሰብ

መ/ ሰዎች እምነት የማይጣልባቸው መሆናቸውን መረዳቱ

8/ ዮሴፍ ብዙ የችግር ዓመታትን ካሳለፈ በኋላም ወንድሞቹ መጥተው ሰገዱለት፣ በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ያሳያቸው የመሪነት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ **"ቀድሞውኑ ነግሬያችሁ አልነበረም?"** በሚል መንፈስ ወንድሞቹ ላይ ታበየ፣ያለፈ ጥፋታቸውን ሊያሳስባቸውም ሞከረ።

ለ/ ብቃት ክህሎት፣ የማያወላውል የመሪነት ውሳኔና ፍትህ

ሐ/ የእግዚአብሔርን እቅድ በመረዳቱ ርሕራሄ ፣ ይቅር ባይነትና ፍቅር አሳያቸው።

መ/ በቀል የእግዚአብሔር መሆኑን፣ የእግዚአብሔርን እቅድ መረዳቱንና የሰዎችን ደካማነት መቀበሉን።

9/ ያለአንዳች ተስፋ መቁረጥ ለሥራው ያሳየው ትጋት ለፈርዖን ከሰጠው ብልህ ምክር ጋር በአንድነት ሆነው ከዮሴፍ ባሕርያት የሚያሳያቸው ሁለት ነገሮች፡-

ሀ/ ብቃትና አዳዲስ ሃሳቦችን አፍላቂ መሆኑን

ለ/ ለእግዚአብሔር መሰጠቱንና የፖለቲካ እውቀቱን

ሐ/ ታጋሽነትና የአስተዳደር ችሎታውን  መ/ ትዕግሥቱንና ብልህነቱን

10/ ዮሴፍ አንድ የተዋጣለት መሪ ሲኖረው የሚገባውን ዝንባሌ አሳይቷል። የመከራው ጊዜ ከተፈጸም በኋላ ከአንደኛው በቀር ሁሉንም አድርጓል፡-

ሀ/ መኩራራትና በቀልን አልፈለገም

ለ/ ሌሎችን ለመርዳት እግዚአብሔር  የሚጠቀምበት መሳሪያ መሆኑን ተረዳ

ሐ/ በልጅነት ዘመኑ ያያቸውን ሕልሞችና የተነገሩለትን ትንቢቶች ለወንድሞቹ አሳሰባቸው።

11-17/ ለሚከተሉት የመሪነት ባሕርያት ገለጻ ስጥ። በዚህ ትምህርት የተዘረዘሩት ሰባቱ የመሪነት ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው።

- የሌሎችን ስሜት መረዳትና ለሌሎች ማሰብ /Empathy/
- እግብ ላይ መድረስ /ግብን መምታት/
- ለሥራው ወይም ለኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት
- የስሜት እርጋታ /ወላዋይ አለመሆን/
- በቡድን መሥራት- ሥልጣን ለሌሎች ማካፈል
- ቃልና ድርጊትን ማጣመርና እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት

11/ ምንም እንኳ በእርሱ እቅድ መሠረት ሁኔታዎች ባይሳኩለትም አንድ መሪ አንገቱን ቀና አድርጎ የሚሄደው ለምንድነው?--------------------------------

12/ ------------ ከበላዮቻቸውና ከበታቾቻቸው ካሉት ሁሉ ጋር አብረው ለመሥራት የሚያስችል የመሪዎች ችሎታ ነው።

13/ የሌሎችን ስሜት ማወቅ፣ ነገሮችንም ከራሱ እይታ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም እይታ የማየት ችሎታ ------------- ይባላል።

14/ አንድ መሪ ቃሉን የሚጠብቅ፣ ለሌሎች ለሚሰጠው መመሪያ እርሱ ራሱ የሚታዘዝ፣ ሀሳቡንም በግልጽ ለሌሎች ማካፈል የሚችልና ሌሎችንም የሚረዳው ------------- ስለሆነ ነው።

15/ ፊት ለፊቱ ግብ የሚያኖርና ሀሳቡ ላይ እስኪደርስ ድረስ ተግቶ የሚሠራ መሪ---------- ነው።

16/ አንድ መሪ የቡድኑ አካል እንደሆነ ሲያስብ፣ ለሌሎች ፍላጎት ሲጠነቀቅ፣ ከሰዎች ጋር መሥራትም የሚያስደስተው ሆኖ ከተገኘ ያ ሰው ----------- ነው ማለት ነው።

17/ በትጋት የሚሠራ፣ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስችል ዕውቀት ያለው፣ ሌሎችን የሚረዳበት መረጃ ማሰባሰብ የሚችል፣ ራሱንና ሌሎችን የሚመዝንበት ሚዛን ያለው መሪ------- ይባላል።

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

የመመዘኛዎቹ መልሶች የተቀመጡት በቅደም ተከተላቸው መሠረት ያልሆነበት ምክንያት የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ወዲያው እንዳታይ ለማድረግ ነው፣

7/ ለ) ከእርሱ በላይ ያሉ ሰዎችን ሥልጣን ያከብራል

ሐ) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰራ

1/ ሐ) አንድን ዓላማ ፈጸመ 8/ ለ) ዮሴፍ ወደ እሥረኞቹ ሄደ።

2/ሀ 2/ መሪው እቅድ የለውም ለ/ 3) መሪው ዓላማ አለው ሐ/ 1) መሪው እቅድ አለው

9/ ሀ) ከሌሎች ጋር መግባባት የሚችል ሰው ነበር።

3/ለ/ እግዚአብሔር ዓላማውን የሚፈጽምበት የራሱ ልዩ መንገድ አለው፣

መ/ እግዚአብሔር የሚሠራውን አስቀድሞ ያውቃል።

10/ እንዳይረበሹ ነገራቸው፣ የእግዚአብሔርን እቅድ በማሳሰብ አጽናናቸው።

4/ሀ) 3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያ ለ/1) ታሪካዊ ማስረጃ

ሐ/4) መስፈርቶችና ኃላፊነቶች መ/2) የአገልግሎት ስጦታዎች

ሠ/3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያ ረ/1) ታሪካዊ ማስረጃ

11/ "የመሪነት ባሕርያት" ከሚለውን ዝርዝር ጋር መልሶችህን አስተያይ

5/ ሀ/3) ፀባይ ለ/2) ዝንባሌ ሐ/1) ተፈጥሮ መ/1) ተፈጥሮ ሠ/ 3) ፀባይ

12/ሀ2/ እግብ ላይ መድረስ ለ/4) የስሜት መረጋጋት ሐ/5) የቡድን ሥራ

መ/7) ቃልና ድርጊትን በማጣመር እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት

ሠ/1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት ረ/3) ብቁ ሆኖ መገኘት

ሰ/6/ ሥልጣንን ለሌሎች ማካፈል

6/ ዓላማውን ለመፈጸም እግዚአብሔር መሪዎችን ይመርጣል።